# የኢትዮጵያውያኖች ስፖርት ፌዴሬሽን በአሜሪካ ከየት ወደ የት ?

እንደወትሮዬ የእንጀራ ሱሰ ለማብረድ ወደ አንድ ሃበሻ ግሮሰሪ ቆም እንዳልኩ ከአንድ local news paper ፊት ለፊት page ላይ በዋሽንግተን ስለሚደረገው እግር ኳስ ውድድር አንብቤ በትንሽ እንደመሳቅ አልኩና ወድያው ልቤ ሲያዝን ያየው ባለሱቅ ምነው ወንድሜ ብሎ በመገረም ሲያየኝ እኔም ተገርሜ ነው በስፖርቱ ለሁለት መከፈል አልኩት እሱም መልሶ ወዲያው መገረም ያለብህ አንድ ሆኑ ተብሎ ቢፃፍ ነበረ ብሎ አስቆኝ ተለያየን ። እኔ በእውነቱ የማንም ስፖርት ጎራ ደጋፊ አይደለሁም ፡ ኳስ ተጫዋችም አይደለሁም የኳስ ፍቅር ደግሞም የለኝም ሆኖም በየአመቱ ልጆቼንና ባለቤቴን ይዢ የስፖርት በአል በተከበረበት እለት አልቀ ርም ነበር፡ ምክንያቱም ይሄ ጥሩ አጋጣሚ እንደ አሸዋ የተበተኑ ዘመዶቼንና ጓደኞቼን የማገኝበት እንዲሁም የአገሬን ህዝብ አንድ ቦታ የማይበት የአንድነታችን ምልክት ስለነበር ነው። የአብዛኛውም አትዮጵያዊ ሃሳብ ከዚህ ከኔ የተለየ አይመስለኝም ። ከዚህ ቀደም የምሰማው ቤተክርስትያን ተከፈለ የፖለቲካ ድርጅት ተከፈለ ሞቅ ያለው ትዳር ፈረሰ ነበር ።

የአሁኑ ለየት የሚያደርገው ደግሞ ለተከፈለው ጎራ ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ በቼክ አላሙዲ ተሸላሚ መሆኑ ነው ከዚያም አልፎ ለሆዳችም አታስቡ እየተባሉ ነው፡ በእርግጥም “ ለሆዳም በሬ ጭድ ይታዘዝለታል” ይባል አይደል? እስቲ አንድ ግዜ ቆም ብለን እናስብና እራሳችንን እንጠይቅ፡ የኢትዮጵያ ፌዴሬሼን ሲቋቋም በማን ገንዘብ ነበር? ለዚህ ሁሉ አመታትስ ደምቆ መከበር ያበቃው ማን ነው ? በእርግጥም በእኛ ኢትዮጵያዊያኖች ብቻ ነው። ስለዚህ መታወቅ ያለበት በፊትም ቢሆን በእራሳችን ወጭ ለአለፉት አመታት እንዳከበርነው አሁንም ያለማንም እርዳታ መቀጠል እንችላለን፡ ይልቁንስ በእኛ ስም ክብራቸውንና ሞራላቸውን ሸጠው ለመክበር ለሚፈልጉ ግለሰቦች ሌላው ኢትዮጵያዊ ትብብር እንደማያደርግ አምናለሁ።

ኢትዮጵያ ለዘለአለም ትኑር !

ገረመው አስፋው ከሲያትል